የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ የካቲት ፲፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.44
ADDIS ABABA 19th February , 2016

አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ……………………………………………………..ገጽ ፰ሺ፰፻፷፩

Proclamation No. 923/2016

Ethiopia's Overseas Employment Proclamation ………………………………………Page 8861

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰

## Proclamation No. 923/2016

### <u>የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት የወጣ አዋጅ</u>

### ETHIOPIA'S OVERSEAS EMPLOYMENT PROCLAMATION

መሥራት ለሚችሉ ዜጎች ሁሉ በአገር ውስጥ ምቹ የሥራ ዕድሎች የሚስፋፉበትን ሁኔታ ለመፍጠር መንግሥት የሚያደርገው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ውጭ አገር በመሄድ ለመሥራት ፍላጎት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን መብታቸው፣ ደህንነታቸው እና ክብራቸው ተጠብቆ ባላቸው ችሎታና አቅም ሠርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHEREAS, the Government's commitment to create a favorable domestic condition for promoting employment opportunities for those who are able to work is intact, it has been found necessary to protect the rights, safety and dignity of Ethiopians who are willing to take-up overseas employment in pursuance of their qualifications and ability;

ከተቀባይ አገሮች ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት መፈራረም ሕጋዊ የውጭ አገር ሥራ ስምሪትን በማጠናከር ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል ጠቃሚ መሆኑ በመታመኑ፤

WHEREAS, it is believed that bilateral agreements with receiving countries may strengthen lawful overseas employment and could prevent human trafficking;

የግሉ ዘርፍ በውጭ አገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥ ሊኖረው የሚገባውን ተሳትፎ በሕግ መወሰን በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it has become necessary to define the role of the private sector in overseas employment exchange services;

መንግሥት በውጭ አገር ሥራ ስምሪት አፈጻጸም የሚኖረውን የክትትልና የቁጥጥር ሚና ከፍ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it has become essential to enhance the role of the Government in the follow-up and monitoring of overseas employment exchange services;

በሥራ ላይ የነበረውን የሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ በአዲስ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት ሕግ መተካት አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHEREAS, it has become necessary to replace existing Employment Exchange Services Proclamation with new Overseas Employment Proclamation;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፦

፩/ "የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ" ወይም "ኤጀንሲ" ማለት መንግሥታዊ አካል ያልሆነና ከሠራተኛ ጋር የሥራ ውል ስምምነት በማድረግ ሠራተኛን በውጭ አገር ለሥራ ለአሠሪ የማቅረብ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው፤

፪/ "ፈቃድ" ማለት በሚኒስቴሩ ለኤጀንሲ የሚሰጥ በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ነው፤

፫/ "አሠሪ" ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በዚህ አዋጅ በተመለከተው የሥራ ውል መሠረት በኤጀንሲ አማካኝነት፣ መንግሥት-ለመንግሥት በሚደረግ ስምምነት ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በቀጥታ ቅጥር የሚያሰራ ሰው ነው፤

፬/ "ሠራተኛ" ማለት በዚህ አዋጅ በተመለከተው የሥራ ውል መሠረት ከአሠሪ ወይም ከኤጀንሲ ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ሲሆን፣ እንደአግባቡ ሥራ ፈላጊንም ይጨምራል፤

፭/ "ቀጥታ ቅጥር" ማለት የመንግሥታዊ አካል ወይም የኤጀንሲ አገልግሎት ሳይሰጥ አሠሪውና ሠራተኛ በራሳቸው በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈፀም ቅጥር ነው፤

፮/ "የሥራ ሁኔታ" እና "የሥራ ላይ አደጋ" ማለት በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይኖራቸዋል፤

፯/ "የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ" ማለት አንድ ሠራተኛ ለሚቀጠርበት ሥራ የመሥራት ብቃት ያለው ስለመሆኑ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝኖ የሚሰጥ ማስረጃ ነው፤

hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Ethiopia's Overseas Employment Proclamation No. 923/2016".

2. **Definition**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "Private Employment Agency" or "Agency" means any person other than a Government body, which makes a worker available to an overseas employer by concluding a contract of employment with such a worker;

2/ "license" means a certificate of competence issued by the Ministry to an Agency enabling the latter to engage in providing overseas employment exchange services;

3/ "employer" means any person who employs one or more persons through an Agency or through Government to Government arrangement or through direct employment in accordance with this Proclamation;

4/ "worker" means an individual who has a contractual relation with an employer or an Agency in accordance with this Proclamation and it may, as the case may be, include a job-seeker;

5/ "direct employment" means an employ ment relationship between an employer and a worker without the involvement of a Government organ or an Agency;

6/ "condition of work" and "occupational accident" shall have the meanings provided for under Labour Proclamation;

7/ "certificate of occupational competence" means a document issued by an authorized organ evidencing that the worker is capable of performing a particular task;

8/ "family" means a spouse, ascendants, descendants or relatives up to a second

፰/ “ቤተሰብ” ማለት የትዳር ጓደኛ፣ ወላጅ፣ ተወላጅ ወይም እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ ነው፤

፱/ “የሁለትዮሽ ስምምነት” ማለት የውጭ አገር የሥራ ቅጥር አስመልክቶ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በተቀባይ አገር መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፤

፲/ “ሚኒስቴር” ማለት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፤

፲፩/ “አግባብ ያለው ባለሥልጣን” ማለት በክልል የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎችን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፪/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፫/ “ሚሲዮን” ማለት በውጭ ሀገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን፣ ቋሚ መልእክተኛ ጽሕፈት ቤት፣ ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ወይም የንግድ ጽሕፈት ቤት ነው፤

፲፬/ “ንግድ ማህበር” ማለት የሽርክና ማህበር፣ የአክሲዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ነው፤

፲፭/ “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፮/ በወንድ ጾታ የተገለጸው ማንኛውም አገላለፅ ሴትንም ይጨምራል፡፡

**፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ ፦

፩/ በመንግሥታዊ አካል፣ በኤጀንሲ አማካኝነት ወይም በቀጥታ በሚደረግ ቅጥር የኢትዮጵያዊያን የውጭ አገር ሥራ ስምሪት ግንኙነት ላይ፣

፪/ ለትርፍ በሚካሄድ ሥራ ላይ ላልተመሠረተ ለቤት ሠራተኛነት ለመቀጠር ወደ ውጭ አገር በሚሄድ ኢትዮጵያዊ ላይ፣

ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በመንግሥት ስለሚሰጥ የሥራ ስምሪት አገልግሎት

### ንዑስ ክፍል አንድ

degree through consanguinity or affinity;

9/ “bilateral agreement” means an agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the receiving country pertaining to overseas employment;

10/ “Ministry” means the Ministry of Labour and Social Affairs

11/ “appropriate authority” means a Regional Government organ entrusted with the power to implement labour laws;

12/ “region” means any Regional State specified under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

13/ “mission” means Ethiopia’s diplomatic mission, permanent mission, consular office or trade office abroad;

14/ “business organization” means a partnership, share company or private limited company;

15/ “person” means any natural or juridical person;

16/ any expression to the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Proclamation shall apply to:

1/ overseas employment relation of Ethiopians’ conducted by public employ ment organs, through Agency or on direct employment;

2/ Ethiopians travelling to abroad to engage in overseas contracts of house maid service for non-profit making purposes.

## PART TWO

## PUBLIC EMPLOYMENT EXCHANGE SERVICE

### SECTION ONE

### EMPLOYMENT EXCHANGE SERVICE

**4. <u>Recruitment and Placement of Worker</u>**

## ስለሥራ ስምሪት አገልግሎት

### ፬. የሠራተኛ ምልመላና ስምሪት አገልግሎት

፰ሺ፰፻፰፬ ኒስቴሩ መንግሥት ለመንግሥት በሚደረግ ..ምነት መሠረት በተቀባይ አገር ለሚገኝ መንግሥታዊ ድርጅት የሠራተኛ ምልመላና ስምሪት አገልግሎቶችን ሊሰጥ ይችላል፡፡

### ፭. ስለአገልግሎት ዓይነቶች

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት በሚኒስቴሩ የሚሰጡ የሠራተኛ ምልመላና ስምሪት አገልግሎቶች ቃለ መጠይቅና መረጣ ማድረግን፣ የጤና ምርመራ እንዲከናወን ማድረግን፣ የሥራ ውል ማፅደቅን፣ የቅድመ-ቅጥር እና ቅድመ-ጉዞ ገለፃ መስጠትን፣ የተቀጣሪ ሠራተኛ የውጭ ጉዞ ማመቻቸትን እና የመሳሰሉትን ሌሎች አገልግሎቶች ይጨምራል፡፡

### ፮. ቀጥታ ቅጥር የተከለከለ ስለመሆኑ

፩/ ማንኛውም አሠሪ በሚኒስቴሩ ወይም በኤጀንሲ በኩል ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ ሠራተኛን መልምሎ ሊቀጥር አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ በሚከተሉት ሁኔታዎች ቀጥታ ቅጥር ሊፈቅድ ይችላል፦

- ሀ) አሠሪው የኢትዮጵያ ሚሲዮን አባል ከሆነ፤
- ለ) አሠሪው ዓለም አቀፍ ድርጅት ከሆነ፤ ወይም
- ሐ) ከየቤት ሰራተኛነት ቅጥር በስተቀር ማንኛውም ሥራ ፈላጊ በራሱ ጥረት የሥራ ዕድል ሲያገኝ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) መሠረት በቀጥታ የሚደረግ ቅጥር በሚኒስቴሩ ሊፈቀድ የሚችለው ፦

- ሀ) ሠራተኛው በሚሄድበት አገር መብቱ፣ ደህንነቱና ክብሩ ሊጠበቅ እንደሚችል በሚመለከተው ሚሲዮን ወይም በተቀባዩ አገር ሚሲዮን ከሌለ አዲስ አበባ በሚገኘው የተቀባዩ አገር ሚሲዮን እና በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ፣

The Ministry may provide recruitment and placement services to Governmental organization in receiving country based on Government to Government agreement.

### 5. Types of Services

The services to be provided by the Ministry pursuant to Article 4 of this Proclamation shall include interviewing and selection; causing medical examinations; approval of employment contracts, provision of pre-employment and pre-departure orientations, facilitation of departure of employed workers and other similar services.

### 6. Prohibition of Direct Employment

1/ No employer shall directly recruit and employ a worker except through the Ministry or an Agency.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, the Ministry may permit direct employment on the following grounds:

- a) where the employer is a staff of an Ethiopian Mission;
- b) where the employer is an International organization; or
- c) where the job seeker acquires a job opportunity by his own accord in job positions other than house maid service.

3/ The direct employment pursuant to paragraph (c) of sub-article (2) of this Article may be permitted by the Ministry only when evidence of the following are secured:

- a) an assurance secured from a pertinent mission or from mission of country of destination if an Ethiopian mission is not present in the country of destination; and the Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia that the worker's basic rights and dignity will be respected in the country of destination;
- b) life and disability insurance coverage for the worker pursuant to Article 62(1) of this Proclamation has been issued;
- c) appropriate air or land transport service together with contract of employment are submitted.

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ (፩) መሠረት የተገባ የሕይወትና የአካል ጉዳት ካሣ ኢንሹራንስ ሽፋን ስለመኖሩ፣ እና

ሐ) ከሥራ ውሉ ጋር ምቹ የሆነ የአየር ወይም የየብስ መጓጓዣ አገልግሎት የሚያገኝ ስለመሆኑ፣

፳ሺ.፳፻፳፫ ማስረጃ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ቀጥታ ቅጥር እንዲፈፅም ለተፈቀደ ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ሊወጣ የሚችለው በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን በኩል ብቻ ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ትምህርት፣ ሥልጠና እና የጤና ምርመራ

### ፯. ስለ ትምህርት ደረጃና የሙያ ብቃት ምዘና

፩/ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ማንኛውም ሠራተኛ ፦

ሀ) ቢያንስ የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀ፣ እና

ለ) በሚቀጠርበት የሥራ መስክ አግባብ ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ የያዘ፣

መሆን አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሠራተኛው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚጠየቀው አሠሪው የሚጠይቃ ቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

### ፰. ስለ ግንዛቤ ማሳደጊያ ፕሮግራም

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ፦

፩/ ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለመሄድ ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ስለተቀባይ አገር ሁኔታ፣ በሚሰማሩበት የሥራ መስክ ሊኖራቸው ስለሚገባ ክህሎት፣ ስለመብታቸውና ኃላፊነታቸው እና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች የቅድመ-ስምሪትና የቅድመ-ጉዞ ግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠና በመደበኛነት ይሰጣል፤

4/ An advertisement to vacant positions permitted for direct employment pursuant to this Article shall only be conducted through the Ministry or the appropriate authority.

## SECTION TWO

## EDUCATION, TRAINING AND MEDICAL EXAMINATION

### 7. Educational level and Occupational Competence Assessment

1/ Any worker who desires to take-up overseas employment shall:

a) at least complete eighth grade education;

b) possess a certificate of occupational competence issued by the appropriate competence assessment center for the work he is to be employed.

2/ The worker shall be required to present certificate of occupational competence pursuant to sub-article (1) of this Article only when the fulfillment of other requirements set by the employer are ascertained.

### 8. Awareness Raising Program

The Ministry or the appropriate authority shall:

1/ undertake regular pre-employment and pre-departure awareness raising to citizens who show interest to take-up overseas employment pertaining to the conditions of receiving countries, the required skill for a job position they are taking, their rights and duties and similar other matters;

2/ conduct continuous national awareness raising activities to the public at large by using mass media and disseminating correct and up-to-date information regarding overseas employment.

3/ conduct regular awareness raising programs to Agencies' board of directors, general managers and employees on issues related to overseas employment;